በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic Of Ethiopia
Ministry Of Trade & Regional Integration

ቀን/Date: መጋቢት 18 2014
ቁጥር/No: ሀ11-229/922

ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
ለፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን
ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
ለዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል
ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- **የመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን ይመለከታል፣**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 23 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የነዳጅ ምርቶች ዋጋ በየወሩ እንዲከለስ ውሳኔ ማሳለፉ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሰረት **ከየካቲት 19/2014 ዓ.ም እስከ መጋቢት** 30/2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ በተመለከተ የተዘጋጀ መግለጫ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገብረመስቀል ጫላ ምጣሎ
ሚኒስትር

አባሪ- 1 ገጽ

እንዲያውቁት
- ለክቡር የንግድ አሠራርና ላይሰንሲንግ ዘርፍ ሚንስትር ዴኤታ
  ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

ግልባጭ፡-
- ለነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦትና ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን
  አዲስ አበባ
- ለህዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት
- ለንግድ ዕቃዎች ዋጋ ጥናት፣ ክትትል እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት
  ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

Tel. +251-5-527676
Fax. +251-5-501697
P.o.Box: 704
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# የመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች መሸጫ ዋጋን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 23 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የነዳጅ ምርት ዋጋ በየወሩ እንዲከለስ በሰጠው መመሪያ መሰረት ከየካቲት 19 እስከ መጋቢት 30/2014 ዓ.ም ተግባራዊ የሚሆን የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን አስመልክቶ ይህ መግለጫ ተዘጋጅቷል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የዓለም የነዳጅ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የሚገኝ ሲሆን መንግስት የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫናን ለመቀነስ ሲል የነዳጅ ምርትን ከገዛበት ዋጋ በግማሽ ለህብረተሰቡ በሽያጭ እየተላለፈ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ይህ የዋጋ ልዩነት በየጊዜው እየተደመረ ከ102 ቢሊየን ብር በላይ የደረሰ ሲሆን ይህም በመንግስት ላይ ከፍተኛ የዕዳ ጫና እያስከተለ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በየአመቱ ለነዳጅ ምርት መግዣ ከ3 ቢሊየን ዶላር በላይ ወጪ እየወጣ በውድ ዋጋ የሚቀርበው የነዳጅ ምርት የአጠቃቀምና የግብይት ሂደት ሰፊ ችግሮች የሚስተዋሉበት ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል ህብረተሰቡ ምርቱን በከፍተኛ ቁጠባ የመጠቀምና የግል አሽከርካሪዎችም ተሽከርካሪዎቻቸውን በተመጣጠነ አኳኃን በማንቀሳቀስ ብዙኃን ትራንስፖርትን የመጠቀም ልምድ ሊያዳብሩ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ የሚታየውን ህገ-ወጥ የነዳጅ ምርት ዝውውርና ኮንትሮባንድ ተግባራት መከላከልና እርምጃ መውሰድ መንግስት ብቻ የሚወጣው ባለመሆኑ ሁሉም የህብረሰብ ክፍል በነዳጅ ምርቶች ግብይት ላይ የሚፈጸሙ ህገ-ወጥ ተግባራትን በመጠቆምና በማጋለጥ በየደረጃው ካለው የጸጥታ አካል ጋር በትብብር ሊሰራ ይገባል፡፡

ስለዚህ መንግስት የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የኢኮኖሚዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲቀጥል ለማስቻል ከየካቲት 19 እስከ መጋቢት 30/2014 ዓ.ም ከቀላል ጥቁር ናፍታ ፣ከባድ ጥቁር ናፍታ እና ከአይሮፕላን ነዳጅ በስተቀር ሌሎች የነዳጅ አይነቶች ባሉበት እንዲቀጥል የተወሰነ መሆኑን እያሳወቅን በአለም ገበያ የሚኖረው የነዳጅ ዋጋ መነሻ በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችል መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት